**አጭር ቃለ ምልልስ ከወ/ሮ ውሂብ ዘውዴ ጋር**

ከ12 ዓመታቸው ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ኳየር ውስጥ በማገልገል ላይ አሉ። የሦስት ልጆች እናትና የሦስት የልጅ ልጆች አያት ናቸው። ለመዘምራን አገልግሎት ያላቸውን ከፍተኛ ቦታ እንዲህ ሲሉ ይገልጣሉ። “ኳየር ለአንድ አገልግሎት ወይም ቤተ ክርስቲያን ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው አምናለሁ። ኳየር የቡድን አገልግሎት ነው ብዙ ሰዎች ከተለያየ የህይወት ክፍል፣ ከተለያየ የህይወት አቅጣጫና ከተለያየ እድሜ ተሰባስበው አንድ ላይ የሚሰጡት አገልግሎት ስለሆነ የኳየር አገልግሎት የሃይል ግምጃ ቤት ነው። የተለያዩ ሰዎች ስለሚገኙበት ዝማሬውም እንዲሁ የተለያየ ይሆናል የማስተማር ስጦታ ያላቸው የሚያስተምር ዝማሬን ሲያመጡ፣ የማበረታታት ስጦታ ያላቸው በርቱ አይዞአችሁ ድሉ የእናንተ ነው ሲሉ፣ የወንጌል ሸክም ያላቸው ደግሞ ካልዳኑት የሆኑ ዝማሬዎችን ያመጣሉ። እነዚህ የተለያዩ መዝሙሮች በተለያዩ ሙዚቃዎችና የተዋቡ ድምጦች ታጅበው ሲዘመሩ መንፈስን ያድሳሉ” ይሉናል። እኛም ስላሳለፉት የአገልግሎት ዘመንና ስለዝማሬ ስላላቸው እይታ አወያይተናቸዋል።

**ስለመንፈሳዊ ዝማሬ ያሎትን ግንዛቤ ቢነግሩን**

ዝማሬ የነፍስ ቋንቋ ነው። በዘመናት መካከል ያለፉ ሰዎች ሁሉ ዘምረዋል አዚመዋል። ስለ እግዚአብሔር አማኞች ያላቸውን ጥልቅ ስሜት ለመግለጥ ተቀኝተዋል። በተለይ ብሉይ ኪዳንን ስናጠና ዝማሬ ከጌታ ጋር ላለ ግንኙነት ትልቅ ቦታ እንዳለው እንረዳለን። ለምሳሌ፦ በሰለሞን ቤተ መቅደስ ውስጥ መዘምራን ሲዘምሩ የእግዚአብሔር ክብር ወርዶ ነበር፣ መዝሙረኛው ዳዊት አማኞችን ለዝማሬ ሲጋብዝ ብዙ ቦታ እናየዋለን፣ ደግሞም ነብያት ለአገልግሎታቸው የዝማሬ አገልግሎትን ጌታን ለመገናኘት እንዲረዳቸው ሲጠይቁ እናያለን። በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ ነው ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ እንኳን ሳሉ ሲዘምሩ የታሰሩበት ሰንሰለት እስኪበጠስ ድረስ የእግዚአብሔር ክብር ሲገለጥ እናያለን። ደግሞም ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቱ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ በመንፈሳዊ ቅኔም እርስ መርሳችሁ ተነጋገሩ ብሎ ክርስቲያኖችን ያሳሰበበት ቦታ አለ። ይህም በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት አንዱ ውጤት ዝማሬ እንደሆነ እናያለን። ዝማሬ ባጠቃላይ በክርስቲያኖች ሕይወትና ጉዞ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዳለው እረዳለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ወደመስቀል ከመሄዱ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደዘመረ በወንጌል ላይ እናገኛለን። ስለዚህ ክርስቲያኖች እንደክርስቲያንነታችን ከምንለማመዳቸው ልምምዶች ውስጥ አንዱ ዝማሬ ነው እላለሁ።

**ሕይወቶትን ለጌታ በሰጡበትና የዝማሬን አገልግሎት በጀመሩበት ዘመን ስለነበረው የአምልኮ ሁኔታ ምን ሊያካፍሉን ይወዳሉ?**

ዘመኑ ምንም ቢርቅም ደግሞም ብዙውን ወዲያው ለማስታወስ ቢያዳግተኝም በዘመናችን በነበረው እንቅስቃሴ ብዙዎቻችን ብላቴናዎች ነበርን። አብዛኞዎቹ ጉባኤ ላይ እንዘምራቸው የነበሩት መዝሙሮች ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ነበሩ አንዳንድ መዝሙሮቻችን ደግሞ አዝማቶች ይሆኑና በተለያዩ ቋንቋዎች እንዘምራቸው ነበር በእውነቱ ትርጉሙ ትክክል ይሁን አይሁን የሚያውቅ ብዙም አልነበረም። ከብሔር ብሔረሰብ ቋንቋ እስከ ፈረንሳይኛና ጣልያንኛ ትርጉም መዝሙሮች እንዘምር ነበር። ሌላው በጉናኤ መካከል እንደ አሁኑ ዘመን ጥሩ ድምጽ ያለው ተመርጦ አልነበረም የሚዘምረው፣ ማንም መዝሙር አለኝ ቢል ለፕሮግራሙ መሪ ቀድሞ ይነግረውና ቦታው ይሰጠው ነበር። ታዲያ ምን አይነት ድምጽ ሊሰማ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ቢሆንም ግን በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርከን ነበር። አሁን ዞር ብዬ ሳየው የነበረን እድሜና እንጽፋቸው የነበሩት መዝሙሮች የማይገናኙ ነበሩ፣ በነገር ሁሉ ይረዳን የነበረው እግዚአብሄር እንደነበር እረዳለሁ። አስታውሳለሁ መጀመሪያ የጻፍኩት መዝሙር መንገዱ ሸካራ ነው የሚል ነበር። በዚያን ጊዜ እንደዚያ የሚያስብል ምንም ነገር ሳይኖረኝ ነገር ግን ከዚያ በኃላ ለኖርኩት ሕይወት ልክ እንደ ትንቢት እንደዘመርኩት እረዳለሁ። አንድ ላይ ስንዘምር የነበርነው ከ 12 - 16 ዓመት ዕድሜ ያለን ልጆች ነበርን ቢሆንም ግን ሁላችን ጌታ በሰጠን ጸጋ መዝሙር እንጽፍ እናገለግልም ነበር እግዚአብሔርም ይባርከን ነበር። ከዚህ የምረዳው ሰው በስፍራው ይገኝ እንጂ ስራውን የሚሰራው እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ነው።

**በሃገራችን በድሮና በአሁኑ ዘመን ባሉ ዝማሬዎች መካከል ምን ልዩነት አለ ብለው ያስባሉ?**

የአማኞች የሕይወት ትግልና የኑሮ ሁኔታ አይነቱ ይለያይ እንጂ በዘመናት መካከል ያው ነው። አባቶቻችን ስለእምነታቸው በአንበሶች ጉድጓድ ይጣሉ ነበር፣ በየዘመናትም ጌታን የሚሉ ሁሉ በተለያየ መገፋትና መከራ ውስጥ ያልፋሉ ጠላትም ሰው እንደመሆናቸው የሚያመጣባቸው ጥርጥርና መከራ ቢኖርም ክርስቲያኑ እንዲበረታና ከጥርጣሬ እንዲወጣ እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ሕዝቡን እንዴት ከጭንቀታቸው እንዳወጣቸው መዝሙራት ይነግሩናል። ደግሞም ዘማሪው በተረዳው መጠን ስለእግዚአብሔር ማንነት ይመሰክራል። በዚህ ረገድ ብዙ ልዩነት አላይም። ጎልቶ የሚታየው ልዩነት ግን ሙዚቃው ነው። የኪቦርድ መምጣት ብዙ ነገሮችን እንደለወጠ ይሰማኛል። የሙዚቃ ቅንብር እጅግ ተለውጧል ማባዣና ማከፋፈያው አድጓል በሲዲና በቴፕ በቀላሉ መዝሙሮችን ማግኘት ስለሚቻል ሕዝቡ በቀላሉ መዝሙሮችን ይለምዳል። በዚህ ዘመን መዝሙሮች በየቤተክርስቲያኑ የሚዘመሩት ልክ ዘማሪው እንደሚዘምረው ነው ። በኛ ጊዜ ከአንዱ ወደ አንዱ ቤተ ክርስቲያን እየሄድን ስለነበር መዝሙሮችን የምንለምደው ዜማዎቹ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ትንሽ ልዩነት ነበራቸው። ስለዚህም የቴክኖሎጂው ማደግ ለመዝሙር መስፋፋት አይነተኛ ሚና

ተጫውቷል። ሌላው የዜማ አይነቶች መብዛት ነው። ድሮ በጣም የተወሰኑ የዜማ አይነቶች ነበሩ ለመዝሙር ስንጠቀምባቸው የነበሩት አሁን ግን በዛ ያሉ ልዩ ልዩ ዜማዎችን እንሰማለን።

**ለአዲሱና ለቀጣዩ ትውልድ ስለዝማሬ አገልግሎት የሚሉት ነገር ይኖራል?**

ትልቁ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮና ሃላፊነት እውነተኛው ወንጌል፣ ከክርስቶስ እንዲሁም ከቅዱሳን አባቶች የተቀበለችውን እውነት ሳይበረዝና ሳይለወጥ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ነው። ሰይጣን ደግሞ ሁል ጊዜ ባለፈው ስለተሰራው ስራ ግድ የለውም ሁል ጊዜ የሚመጣውን ትውልድ ማግኘት ነው የሚፈልገው። ክርስትና ያለፈ ታሪክ ሆኖ ቢቀር ደስታውን አይችለውም የቤተክርስቲያን ደግሞ ሃላፊነት ይህ እንዳይሆን ነው። ተተኪው ትውልድ የእግዚአብሔርን ማንነትና ክብር አውቆ ጌታን ሲያገለግል ማየት እጅግ የሚያስደስት ነገር ነው። የድሮዎቹ ብቻ ዘምረውና አገልግለው ቢቀርና ቢያልፉ ምን ትርጉም ይሰጣል? የጌታ ነገር ወደሚቀጥለው ትውልድ ማለፉን ማየት ከምንም የተለየ ደስታ ይሰጣል። የድሮው ክርስቲያንና የቤተክርስቲያን ሃላፊነት ብዬ የማስበው መመሪያ መስጠት፣ መንገድን ማሳየት፣ በትክክል መምራት ነው ብዬ አስባለሁ። ወጣቱን የዝማሬ አገልግሎት ተቀብሎ በትጋት ሲሮጥ ማየት እጅግ የሚያስደስት ነገር ነው። እኔም ለተውላቸው የምወደው ምክር የአገልግሎታቸውን መነሻ ዋና ማዕከል በትክክል መለየት ነው። ሁል ጊዜ እግዚአብሔር የልብን ነው የሚመለከተው ስለዚህ ለምንድን ነው የማገለግለው? ለሚለው ጥያቄ ጥሩ መልስ መመለስ ይጠበቅብናል። እግዚአብሔርን የምናገለግለው ለእርሱ ክብር ነው መልሳችን ይህ እስካልሆነ ድረስ ራሳችንን እየመረመርን መስተካከል አለብን። ሌላው ለግል ሕይወት ጥንቃቄ ማድረግ ነው። ከተዳከመና ከቀጨጨ አገልጋይ ውስጥ የተዳከመ አገልግሮት ነው የሚወጣው። የግል ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ማሳለፍ፣ ቃሉን ማንበብ፣ መፀለይ፣ መልካም ቃል የሚሰጥበት ቦታ ሄዶ መማር፣ ከሌሎች ጋር ሕብረት ማድረግና ማምለክ ደግሞም ለአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ራስን አሳልፎ በመስጠት ለዕድገታችን ትልቅ ቦታ አለው። መዝሙሮቻችን በቃሉ ላይ የተመሰረቱ ቢሆኑ ቃሉ በዘመናት መካከል አይለወጥምና ዝማሬዎቻችንም ዘመናትን የሚሻገሩ ከጆሮ የሚጥም ብቻ ሳይሆን ውስጥንም የሚሰሩ ይሆናሉ። የሚዘምረውን በሚያውቅና ተለማምዶ በሚዘምር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ስለዚህም ይህ ትውልድ ይህን ልብ እንዲል እመክራለሁ።